# ከኃላፊነት ለሚነሱና ት/ቤት ለሚገቡ ተሿሚዎች የስራ ምደባና ደመወዝ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ እና ሰርኩላሮች

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABAB
PUBLIC SERVICE AND HUMAN

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
## የከንቲባ ጽ/ቤት
## CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
### Office of the Mayor

ቀን 2/6/12
Date

E-13-118
5/06/12

ቁጥር ፈ/ፈ/ደ0/12-6
No.

ለፋይናንስ ቢሮ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>ምደባ ያላገኙ አመራሮች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ክፍያን ይመለከታል</u>፡፡

ከላይ በርእሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምደባ ያላገኙ አመራሮች የመጀመሪያ ሦስት /3/ ወር ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲከፈላቸው እና ከሦስት /3/ ወር በኋላ ደግሞ የወር ደመወዛቸው ብቻ ባለው አሠራርና መመሪያ መሠረት ክፍያ እንዲፈፀም መልዕክቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዳዊት ምንዳዬ ገ/ፃዲቅ
የከንቲባ ጽ/ቤትና
የካቢኔ ጉዳዮች ም/ኃላፊ

<u>እንዲያውቁት</u>//
- ለክቡር ም/ከንቲባ

<u>ግልባጭ</u>//
- ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ
  <u>አዲስ አበባ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መዝገብ ቤት
ፋይናንስ ቢሮ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
City Government of Addis Ababa

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፋይናንስ ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINSTRAION
BUREAU OF FINANCE

ቀን 06/06/2012 ዓ.ም ቁጥር ፋ/ቢ/-ፖ-5/ፊዊ-/1322

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

- ለአራዳ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለልደታ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለየካ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ምደባ ያላገኙ አመራሮች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ክፍያን ይመለከታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በቁጥር አአ/ከፅ/17/11/178 በቀን 02/06/12 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ምደባ ያላገኙ አመራሮች የመጀመሪያ ሶስት ወር (3 ወር) ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲከፈላቸው እና ከሶስት ወር (ከ3 ወር) በኋላ ደግሞ የወር ደመወዛቸው ብቻ ባለው አሰራርና መመሪያ መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም መልእክቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፍ አሳስቦናል።

በዚሁ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን እያስታወቅን ከንቲባ ጽ/ቤት የላከልንን ደብዳቤ አንድ ገጽ ኮፒ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር!

(ማህተም: የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ / Addis Ababa City Administration Bureau of Finance)

(ፊርማ) የፋይናንስ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ፡-

- ለቢሮ ኃለፊ
- ለምክትል ቢሮ ኃላፊ (ፋይናንስ ዘርፍ)
- ለምክትል ቢሮ ኃላፊ (በጀት ዘርፍ)
- በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ ለቢሮ አማካሪ

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ

Addis Ababa City Administra
Public Service & Human Reso
Development Bu

ቁጥር 03-ጠ11-24-74-645
Ref.No

ቀን 1-7-2012
Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

- ለአራዳ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአዲስ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ከሹመት ተነስተው በሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ላይ የሚመደቡት'' በተመለከተ ማስተካከያ ስለማስተላለፍ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በ ጥር 5/2012 ዓ.ም በቁጥር 03-ጠ11-24/30/350 በተለያየ ምክንያት ከሹመት የሚ አመራሮች አመዳደብ በተመለከተ የተላለፈ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም መመሪያ ከተላለፈ በኋላ የተለያየ አፈፃፀም በክ/ከተማና በየተቋማቱ እየታየ በመሆኑ ማስተካ ማስተላለፍ አስፈልጓል፡፡

1ኛ/ ማንኛውም ተሿሚ ከሀላፊነት ሲነሳ ወደ ሲቪል ሰርቪስ መዋቅር በሜሪት ስርዓት ለመመደብ የሚመደብበትን ተፈላጊ ችሎታ በትምህርት ዝግጅትና በስራ ልምድ ማሟላት ይኖርበታል፡፡

2ኛ/ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ቀን በተላለፈው ሰርኩላር ከ2009 ጀምሮ በስራ ላይ የሚገኘውን ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች አመዳደብ መመሪያ እንደተጠበቀ በማድረግ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

"በአዲስ ተስፋ ቀመር የከተማችንን ህዝብ እናገለግላለን !!!"
መልስ ሲፅፉልን የእኛ ቁጥር ጠቅሰው ይፃፉ
አዲስ አበባ Addis Ababa
☎ 011 849 40 90
E-mail: aacscom@yahoo.com
✉ 90

3ኛ/ አምስት ዓመት በአመራርነት ሳይሞላቸው ሲመደቡ ወይም የተመደቡ በቀድሞው መመሪያ መሠረት ምደባ ይሰጣቸዋል እንጂ የደረጃ 15 እና ደረጃ 16 ተጠቃሚ አይሆንም፤

4ኛ/ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ቀን በተላለፈው ሰርኩላር አምስት ዓመት ያገለገለ በሚል የተቀመጠው አምስት ዓመት በሹመት ላይ የቆየ ማለት እንደሆነ እንዲታወቅና ሌሎች ህጋዊ የስራ ልምዶችን በተጨማሪነት በማካተት በሚመደብበት ስራ መደብ ላይ የሚጠይቀውን ልምድ የሚያሟላ ማለት ነው፡፡

5ኛ/ ቀደም ሲል በሲቪል ሰርቪስ ላይ ሆነው ከሀላፊነቱ ሲነሱ በሹመት ሲያገለግሉ ቆይተውበተለያዩ ምክንያቶች ከሀላፊነት ሲነሱ ይዘውት የነበረው የሚሪት ደመወዝ አሁን ከደረጃው የመነሻ ደመወዝ በላይ ከሆነ የበፊቱ ደመወዛቸው ሳይቀንስ በሚመለከታቸው የስራ መደብ ላይ ተመድበው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

6ኛ/ በማዕከል፣ በክ/ከተማ በወረዳ አስተዳደር እርከን ላይ ሲያገለግሉ ቆይተው ከሀላፊነት ለሚነሱ ተሿሚዎች በየነበሩበት እርከን የተወሰነውን ደረጃ አግኝተው በሲቪል ሰርቪስ መዋቅር የሚመደቡ ሲሆን በምደባ ወቅት የአስተዳደር እርከን ለውጥ የሚያደርጉ ከሆነ ሲያገለግሉ በነበሩበት የተወሰነውን ደረጃ ብቻ ያገኛሉ፣

7ኛ/ ይህ ማስተካከያ ተግባራዊ የሚሆነው ከጥር 5/2012 ዓ.ም ጀምሮ በመመሪያው የተመደቡትን ጭምር በማካተት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

8ኛ/ ከኃላፊነት ተነስተው ወደ ሲቪል ሰርቪስ መዋቅር የሚመደቡት አመራሮች መመሪያውና ይህ ማብራሪያ ከወጣበት ከጥር 5/2012 ዓ.ም ጀምሮ ለሚነሱና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ምደባ ሳይሰጣቸው ለቆዩ አመራሮች ብቻ ይሆናል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ

Addis Ababa City Administration
Public Service & Human Resource
Development Bureau

ቁጥር ____________
Ref.No ____________

ቀን ____________
Date ____________

9ኛ/ በካሪየር ስትራክቸር ተጠቃሚ ከነበሩ ለመምህራን፣ ር/መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች እስከ ሁለት አመት ብቻ በሹመት ከቆዩ ወደነበሩበት ሙያቸው ተመልሰው አቻዎቻቸው የደረሱበትን ታሳቢ ተደርጎ የሚመደቡ ይሆናል፣ በተጨማሪም የጤና ባለሙያዎች ከነበሩ አቻዎቻቸው የደረሱበትን የጤና ሙያተኞች ደረጃና ስያሜ ይሰጣቸዋል፡፡ ሆኖም ከአገር አቀፉ የጤና ሙያተኞች ከሚያሰጠው ተዋረድና ደረጃ በላይ የሚያገኙ አይሆንም፡፡

10ኛ/ ይህ ሰርኩላር በሜሪት ሹመት የተመደቡትን የሚመለከት አይደለም፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኃይለ... ...
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u>

- ለሰው ሀብት ስራ አመራር ዘርፍ

<u>አዲስ አበባ</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ

Addis Ababa City Administration
Public Service & Human Resource
Development Bureau

ቁጥር 03-መ/ዘ24/30/3/0
Ref.No

ቀን 5/5/2012
Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፡

- ለአራዳ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአዲስ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በአመራርነት ቆይተው በሜሪት ምደባን በተመለከተ የተላለፈ ሰርኩላር፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴክተር መስሪያ ቤቶች በሹመት ተመድበው ሲያገለግሉ ቆይተው በተለያየ ምክንያት ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ሲደረግ በሥራ ላይ በሚገኘው መመሪያ መሰረት ምደባ እንደሚሰጣቸው ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረት የከተማ አስተዳደሩ በአዲስ መዋቅር ስራ ለውጥ ምክንያት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ የሰራተኞች ድልድል የተደረገ ሲሆን ከፍተኛ የስራ ደረጃዎች በሙሉ ምደባ የተደረገባቸው ሲሆን ነገርግን በተለያየ ምክንያት ከአመራርነት ሲወርዱ ባላቸው የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ መሰረት ክፍት የስራ መደብ ተፈልጎ መመደብ ባለመቻሉ በዝቅተኛ መደብ ላይ ሲመደቡ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር እና የቅሬታ ምንጭ ሆኖ ችግር እየፈጠረ በመሆኑ ምክንያት ችግሩን በማጥናት ከዚህ በታች በተገለፀው መሰረት መመሪያውን በማሻሻል ምደባ እንዲሰጣቸው ተወስኗል፡፡

በማዕከል፣ በክፍለ ከተማና በወረዳ የከፍተኛ የስራ ደረጃ ጀምሮ የሜሪት የሥራ መደቦች በሰራተኞች ተደልድለው የተያዘ በመሆኑ ፤

1. በሹመት ቆይተው ከአመራርነት የሚነሱ አመራሮች በሹመት ላይ ረጅም ጊዜ ያገለገሉና በመንግስት ሥራ የሰጡትን ጊዜ በማገናዘብ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚገኙ ከአምስት ዓመት በላይ የስራ ልምድ ያላቸውና መስፈርቱን የሚያሟሉ ፡-
   - ከማእከል ለሚነሱ በማእከል ለነበሩ በነጥብ የስራ ምዘና ደረጃ 18 ላይ እንዲመደቡና በዚህ ስርአት ላልተካተቱ የተቋሙን የሜሪት ከፍተኛ ደረጃ ምደባ እንዲያገኙ

"በአዲስ ተስፋ ቀመር የከተማችንን ህዝብ እናገለግላለን!!!"
☎ 011 849 40 90
መልስ ሲፅፉልን የእኛ ቁጥር ጠቅሰው ይፃፉ
E-mail: aacscom@yahoo.com
✉ 9092

- ከክፍለ ከተማ ለሚነሱ በክፍለ ከተማ በነጥብ የስራ ምዘና ደረጃ 16 ላይ እንዲመደቡና በዚህ ስርአት ላልተካተቱ የተቋሙን የሚሪት ከፍተኛ ደረጃ ምደባ እንዲያገኙ
- ከወረዳ ለሚነሱ በወረዳ ለነበሩ ያረጃ 15 ላይ እንዲመደቡ ሆኖ በዚህ ስርአት ላልተካተቱ የተቋሙን የሚሪት ከፍተኛ ደረጃ ምደባ እንዲያገኙ በሶስቱም የአስተዳደር እርከኖች መደቦቹ ከሌሉ ለቦታው የተወሰነውን ደመወዝ እያገኙ በሌሎች መደቦች ላይ ተመድበው እንዲሰሩ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለሰው ኃብት ስራ አመራር ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ
  አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት
ልማት ቢሮ

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
PUBLIC SERVICE AND HUMAN
RESOURCE DEVELOPMENT BUREAU

ቁጥር 36፡ጠ11-24-09-107
Ref.No.

ቀን 25-11-2010
Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የአመራር ደመወዝ ማስተካከያ መላክን ይመለከታል፤

ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ለአላማ ፈፃሚ ባለሙያዎች ከከንቲባ ጽ/ቤት የፀደቀውን የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ ተግራዊ እንዲሆን የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት ከባለሙያ እስከ ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ደመወዝን በሚመለከት የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ቀርቦ በየደረጃው ለሚገኙ ተሿሚዎች የተቋም ኃላፊዎች ተግባራዊ እንዲሆን በቁጥር 03-ጠ11-24/74/66 በቀን 12/07/2010 ዓ.ም የአመራር ደመወዝ ማስተካከያ እንዲስተናገድ መላካችን ይታወቃል፡፡

ሆኖም በከተማው አስተዳር ካቢኔ ቀርቦ ለሚገኙ ተሿሚዎች የተቋም ኃላፊዎች ተግባራዊ እንዲሆን በቀን 12/07/2010 ዓ.ም የሚለው በ12/07/2009 ዓ.ም ተብሎ እንዲስተካከል እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት
ም/ቢሮ ሃላፊ

ግልባጭ/-
በሰው ሃብት ሥራ አመራር ዘርፍ
- ለቢሮ ኃላፊ
- ለአደረጃጀትና የሥራ ምዘና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት
  አዲስ አበባ

E-mail-aacscom@yahoo.com

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት
ልማት ቢሮ

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABA
PUBILC SERVICE AND HUMAN
RESOURCE DEVLOPMENT BURE.

ቁጥር ..............
Ref.No. 03:ጠ11-24-13-147

ቀን 18/11/10
Date ..............

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የአመራር ደመወዝን ይመለከታል፤</u>

ከመስሪያ ቤታችን በቁጥር 36-ጠ11-24-41-386 በቀን 18/10/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ አላማ ፈፃሚ ባለሙያዎች በከንቲባ ጽ/ቤት የፀደቀ የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ መላካችን ይወቃል::

በመሆኑም የደመወዝ ስኬል ማስተካከያው ተግባራዊ የሚሆነው ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ከባለሙያ እስከ ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ ሲሆን የአመራር ደመወዝ በሚመለከት በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ቀርቦ በየደረጃው ለሚገኙ ተሿሚዎችና የተቋም ኃላፊዎች ተግባራዊ እንዲሆን በቁጥር 03.ጠ11-24/74/66 በቀን 12/07/2010 ዓ.ም በተወሰነው የአመራር የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ መሠረት የሚስተናገድ መሆኑን እየገለፅን ከዚህ ውጪ ተግባራዊ ለማድረግ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ሲፀድቅ ብቻ መሆኑን በጥብቅ እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

[illegible] ግርማይ ደስታ
ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት
ቢሮ ኃላፊ

<u>ግልባጭ/-</u>

- ለቢሮ ኃላፊ
- ለአደረጃጀትና የሥራ ምዘና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት

<u>አዲስ አበባ</u>

E-mail-accb@telecom.net.et
ፖ.ሣ.ቁ 9092
P.O.Box
ፋክስ 57-36-00
Fax
ስልክ ቁጥር 011-8-49-41-52
Tel. No.

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት
ልማት ቢሮ

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
PUBLIC SERVICE AND HUMAN
RESOURCE DEVELOPMENT BUREAU

ቁጥር 11-ጦ11-24/29/345
Ref.No.

ቀን 27/3/09
Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት
አዲስ አበባ፤

174
4/4/09

ጉዳዩ፡- ከኃላፊነት ለሚነሱና ትምህርት ቤት ለሚገቡ ተሿሚዎች
የተሻለፈ ማሻሻያ መመሪያ ስለመላክ፣

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሚያዝያ 2004 ዓ.ም በወጣው አፈፃፀም መመሪያ ከአሁን በፊት የመንግስት ተሿሚዎች ከኃላፊነታቸው ሲነሱ፣ ወደ ትምህርት ሲላኩ እና ትምህርት አሻሽለው ሲመለሱ የሚመደቡበት ሁኔታ ወጥነት የጎደለው በመሆኑ ችግሩን በማስተካከል ይህን ከኃላፊነት ለሚነሱና ትምህርት ቤት ለሚገቡ ተሿሚዎች የሥራ ምደባና ደመወዝ ለመወሰን የወጣ [illegible] መመሪያ በማዘጋጀት የላክ መሆኑን እየገለጽን፣ ከህዳር 1 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መመሪያውን እንድታሳውቁ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

27/03/09

ግልባጭ፣
በሰው ሃብት ሥራ አመራር ዘርፍ
- ለሰው ኃብት ስራ አመራር ዋና የሥራ ሂደት

አዲስ አበባ፣

# ከኃላፊነት ለሚነሱና ት/ቤት ለሚገቡ ተሿሚዎች የስራ ምደባና ደመወዝ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ

ህዳር / 2009 ዓ/ም

አዲስ አበባ፣

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአሁን በፊት የመንግስት ተሿሚዎች ከኃላፊነታቸው ሲነሱ፣ ወደ ትምህርት ሲላኩ እና ትምህርት አሻሽለው ሲመለሱ የሚመደቡበት ሁኔታ ወጥነት የሌለው በመሆኑ ይታዩ የነበሩትን ግድፈቶችን ለማስተካከልና ለማረም በ2004 ዓ/ም በሚያዝያ ወር ላይ መመሪያ ማዉጣቱ የሚታወስ ነዉ፡፡

መመሪያዉ ሲወጣ የመንግስት ተሿሚዎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከኃላፊነት ሲነሱ ወይም በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በመንግስት ፈቃድና ድጋፍ ትምህርታቸውን አሻሽለው ሲመለሱ እንግልት ሳይደርስባቸው በፐብሊክ ሰርቪሱ የሚሪት የስራ መደብ ላይ መድቦ በማስራት የበኩላቸውን ሙያዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ ተገቢ መሆኑ ቢታመንበትም በአፈፃፀም ላይ ችግሮች ተከስተዋል፡፡

ስለዚህም ይህንን የተከሰተ ችግር ለመቅረፍ ያመች ዘንድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 ዓ.ም አንቀጽ 94 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ይህንን የማሻሻያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ፣

1. አጭር ርእስ፣

   ይህ መመሪያ ከሀላፊነት ለሚነሱ እና ት/ቤት ለሚገቡ ተሿሚዎች የስራ ምደባ እና ደመወዝ ለመወሰን የወጣ የማሻሻያ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አግባብነት ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የማሻሻያ ሰርኩላር ውስጥ፣

   2.1. ‹‹ የከተማ አስተዳደር›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

   2.2. ‹‹ተሿሚ›› ማለት በማንኛውም የመንግስት መዋቅር ውስጥ በከንቲባው ወይም በከተማው ስራ አስኪያጅ ወይም በከተማው ም/ቤት ወይም በክፍል-ከተማው ምክር ቤት ወይም የክፍለ ከተማው ስራ አስፈፃሚ ወይም በወረዳ ምክር ቤት ወይም በወረዳው ስራ አስፈፃሚ የሹመት ደብዳቤ ተሰጥቶት በየደረጃው በሚገኝ የከተማው የአስተዳደር እርከን መ/ቤት ውስጥ በሃላፊነት ቦታ በሹመት የተመደበ እና ከላይ በተዘረዘሩት የተሾሙ አማካሪዎች ማለት ነው፡፡



[Type text]

2.3. ‹‹ የመንግስት መስሪያ ቤት›› ማለት በየትኛውም የአስተዳደር እርከን እራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመ እና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከንግስት በሚመደብለት በጀት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚተዳደር መ/ቤቶች ናቸው፡፡

2.4. ‹‹ ዝቅተኛ የስራ መደብ›› ማለት ጥጉ፣ እጥ እና ጽሂ የስራ መደቦች ማለት ነው፡፡

2.5. ‹‹የስልጠና ወይም የትምህርት እድል ›› ማለት ከአንድ ዓመት በላይ የሚሰጥ የረጅም ጊዜ ስልጠና ወይም ትምህርት ሲሆን እድሉ በመንግስት ታቅዶየተገኘ ወይም በግለሰቦች ጥረት ተገኝቶ ለመንግስት ቀርቦ የተወሰነ ነው፡፡

2.6. ‹‹ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ማለት›› ከሙስና ወንጀልና ውጪ በህመም፣ በአቅም ማጣት፣ ምክንያት ማለት ነው፡፡

2.7. ‹‹ ቢሮ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ነው፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ የማሻሻያ ሰርኩላር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከማዕከለል መስሪያ ቤት ጀምሮ እስከ ክፍለ ከተማና ወረዳ አስተዳደር ስር ባሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚሰሩ የአስተደደሩ ተሿሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

4. **የመንግስት ተሿሚ የነበረ ከኃላፊነቱ ሲነሳ ቋሚ የስራ ምደባ ስለሚሰጥበት እና ስለ ደመወዝ አከፋፈል ሁኔታ**፣

4.1. ከሃላፊነት የተነሳው ተሿሚ ከመሾሙ በፊት የመንግስት ሰራተኛ የነበረ ከሆነ፣

4.1.1 አንድ የመንግስት ሰራተኛ የነበረ በአንድ የምርጫ ዘመን በተከታታይ ሶስት ዓመት እና ከዚያ በላይ በሹመት ላይ ቆይቶ በተለያዩ ምክንያቶች ከሹመት ኃላፊነት ከተነሳ፣

ሀ. በሹሙት ላይ በነበረበት ጊዜ ያሻሻለው የትምህርት ዝግጅት እና በሹመት ላይ እያለ የሰራበትን ጨምሮ ያለው የሥራ ልምድ ከግምት ውስጥ ገብቶ በሚያሟላበት የስራ ደረጃ ላይ ይመደባል፣

ለ. በሹመት ላይ በነበረበት ጊዜ ያሻሻለው የትምህርት ዝግጅት ከሌለ በሹመት ላይ የሰራበት ጊዜና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የስራ ልምዶች ተይዘውለት በሚያሟላበት የሥራ ደረጃ ላይ ይመደባል፣

4.1.2. አንድ የመንግስት ሰራተኛ የነበረ በአንድ የምርጫ ዘመን ከ3 ዓመት በታች በሹመት ላይ ቆይቶ በተለያዩ ምክንያቶች ከሹመት ኃላፊነት ከተነሳ፣

ሀ. ከሹመቱ በፊት የነበረው የስራ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃና የሹመት ቆይታው ጊዜ ብቻ እንደስራ ልምድ ተይዞ ይመደባል፡፡ በሹመት ቆይታው ጊዜ እንደ አዲስ የተመደበበት የስራ መደብ ላይ በመንግስት የተደረገ የደመወዝ ጭማሪ ካለ ወይም የስራ መደብ መነሻ ደመወዝ የተቀየረ ከሆነ እና የተደረገ የደመወዝ ማሻሻያ ካለ ጭማሪዉ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

ለ. ከላይ በዚህ አንቀፅ (ሀ) ላይ የተገለጸዉ ቢኖርም ከሀላፊነት የሚነሳው ተሿሚ ካለዉ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ አንፃር ምደባ የሚሰጠው አስቀድሞ በተፈቀደና ክፍት በሆነ የስራ መደብ ላይ እንጂ አዲስ የስራ መደብ በመክፈት ወይም ያሟሉታል በሚባል ታሳቢ ባልተፈቀደ ክፍ ባለ የስራ መደብ ላይ መመደብ እና ደመወዝ መክፈል ክልክል ነው፡፡

ሐ. ከላይ በዚህ አንቀፅ (ሀ-ለ) እንደተጠበቀ ሆኖ ሰራተኛው በሹመት ቆይታ ጊዜ ያሻሻለው ትምህርት ካለ በትምህርት ዝጅቱ መነሻ ደመወዝ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡ በሜሪት ይዞት የነበረው ደመወዝ ካሻሻለው የትምህርት ዝግጅት መነሻ ደመወዝ በላይ ከሆነ ግን ድሮ በያዘው በሜሪቱ ያገኝ የነበረዉን እያገኘ እንደ አዲስ በተመደበበት የስራ መደብ ይቀጥላል፡

4.1.3. አንድ የመንግስት ሠራተኛ የነበረና ከዝቅተኛ የስራ መደብ ተነስቶ ወደ ሹመት የመጣ ሃላፊ ለ3 ተከታታይ አመታት እና ከዛ በላይ አገልግሎ በተለያዩ ምክንያቶች ከሹመት ኃላፊነት ከተነሳ፣

ሀ. ትምህርቱን ካሻሻለ በሹመት የቆየበት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የስራ ልምዶች ተይዘውለት ባሻሻለው የትምህርት ደረጃ እና ልምዱ መነሻ ደመወዝ ላይ እንዲመደብ ይደጋል፣

ለ. ከ3 ዓመት በታች ያገለገለ እና ትምህርቱን ካላሻሻለ ቀድሞ በነበረበት የስራ መደብ መመለስ ሳያስፈልግ ባለው የትምህርት ደረጃ እና የሹመት ቆይታው ጊዜ ብቻ እንደ ስራ ልምድ ተይዞለት በተገኘዉ ክፍት የስራ መደብ ላይ ይመደባል ከነበረም የተሻሻለው በሹመት ቆይታው ጊዜ መንግስት የደመወዝ ጭማሪ አድርጎ ጭማሪ ታሳቢ ይደረጋል፣

5. ከአዲስ አበባ አስተዳደር ውጪ ለሚመጡ ተሿሚዎች፣

ሀ. ከማንኛውም ክልል እና ከፌዴራል መ/ቤት ወይም የልማት ድርጅት በሹመት ላይ የነበረ ሰው ቀጥታ እንደገና በሹመት ወደ አዲስ አበባ ከመጣ ከላይ አንቀጽ 4.1.1.አንቀጽ 4.1.2.እና 4.1.3. በተዘረዘው መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል፣

ለ. ነገር ግን ከክልል ወይም ከፌዴራል የመ/ቤት ወይም የልማት ድርጅት የመጣው ግለሰብ ቀድሞ ወደ ነበረበት ለመመለስ ከፈለገ እና የቀድሞ መ/ቤቱም ወይም ክልሉ ለመቀበል ፍቃደኝነቱን ከገለፀ ሹመት የሰጠው አካል ከምስጋና ደብዳቤ ጋር ወደ ነበረበት ይላካል

5. ከሹመት የተነሳው ግለሰብ ከመሾሙ በፊት የመንግሥት ሠራተኛ ያልነበረ ከሆነ፣

አንድ ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ውጪ ወይም በግሉ በመሥራት ላይ እያለ ወደ መንግስት ተቋም በሹመት የመጣ ከሆነ፣

ሀ. ከአንድ አመት በላይና ከሶስት ዓመት በታች በሹመት አገለግሎት በተለያዩ ምክንያቶች ከሹመት ከኃላፊነት ከተነሳ በየእርከኑ ባለው ስራ አስፈፃሚ ሲወሰን ባለው የት/ደረጃና የሹመት ቆይታው ጊዜ ብቻ እንደስራ ልምድ ተይዞለት የቅጥር ፎርማሊቲ አሟልቶ በፐብሊክ ሰርቪሱ በሚሪት የስራ ደመወዝ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

ለ. ተሿሚው ለሶስት ተከታታይ ዓመትና ከዚያ በላይ በሹመት ላይ ቆይቶ በተለያዩ ምክንያቶች ከሹመት ኃላፊነት ከተነሣ፣ ከመሾሙ በፊት በነበረበት ድርጅት ወይም ተቋም ያካበተው የሥራ ልምድ፣ ህጋዊነት እየተረጋገጠ በትምህርት ዝግጅቱና በስራ ልምዱ መሠረት የቅጥር ፎርማሊቲ አሟልቶ በፐብሊክ ሰርቪሱ የሚሪት የስራ መደብ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

ሐ. ከላይ ከዚህ አንቀጽ "ሀ" እና "ለ" ላይ የተገለፀውን እንደተጠበቀ ሆኖ ግለሰቡ ቀድሞ ወደ ነበረበት መ/ቤቱ ወይም ተቋም ለመመለስ ከፈለገና የቀድሞው መ/ብቱም ለመቀበል ፈቃደኝነቱን ከገለፀ ሹመት የሰጠው አካል ከምስጋና ደብዳቤ ጋር ወደ ነበረበት ይልካል፡፡

መ. አንድ የቅጥር ፎርማሊቲ ሳይሟላ ከዩኒቨርሲቲ ወይም ምንም ዓይነት ስራ ልምድ ያልነበረው ወደ መንግስት መ/ቤት በቀጥታ በሹመት የተመደበ ባለሙያ የተለያዩ ምክንያቶች ከአንድ ዓመት በላይና ከሶስት አመት በታች አገልግሎ ከሹመት ኃላፊነት ከተነሳ፣ በየእርከኑ ያለው ስራ አስፈፃሚ ሲወስን የቅጥር ፎርማሊቲውን አሟልቶ ከሶስት የትምህርት ደረጃውን መነሻ ደመወዝ እያገኘ እንዲሰራ ይመደባል፣ ነገር ግን ከሶስት ዓመት በላይ በሹመት ካገለገሉ በኋላ የተነሱ ከሆነ በሹመት ላይ የቆዩበት ጊዜ እንደ ስራ ልምድ ይያዝላቸዋል፡፡

ሠ. ከላይ በዚህ አንቀጽ ስር/ሀ-መ/ የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት ስራ ላይ ያልነበረና ቀጥታ ወደ ሹመት የመጣው ግለሰብ ከአንድ አመት በታች አገልግሎበተለያዩ ምክንያቶች ከኃላፊነቱ ከተነሣ በማናቸውም ኃላፊ ውሳኔ ወደ መንግስት ስራ ላይ አይመደብም፣

## 6. የስራ ምደባ ስለመስጠት፤

6.1. ከኃላፊነት የተነሣ ተሿሚ ከኃላፊነቱ እንደተነሳ ወዲያውኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ ምደባ እንዲያገኝ መደረግ አለበት፣ ነገር ግን ተመዳቢው በእጁ ያለውን የመንግስት ኃብትና ንብረት በማስረከብ የተሟላ ክሊንራንስና እንዲሁም ለምደባ የሚያስፈጉ መረጀዎችን በ15 ቀን ውስጥ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፣

6.2. ከኃላፊነት በተነሳው ግዴታውን ባለመወጣት ችግር ምክንያት ምደባ ሣያገኝ የሚዘገይ ከሆነ ለአንድ ወር ብቻ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ሳይጨምር በሹመት ላይ እያለ ይከፈለው የነበረውን ደመወዝ ብቻ መ/ቤቱ እንዲከፈለው የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

6.3. በቀጣዩ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ግዴታውን አሟልቶ ቀርቦ የማይመደብ ከሆነ ግን በትምህርቱ እና በስራ ልምዱ ሊመደብበት በሚያስችለዉ በሚሪት የስራ መደብ ላይ ይመደባል፡፡

6.4. ምደባው የዘገየው በመ/ቤቱ የታወቀ ምክንያት ከሆነ ግን በአንድ ወር ውስጥ ምደባ እንዲያገኝ ይደረጋል ምክነያት ሳይኖረው በመስሪያ ቤቱ ቸልተኝነት ምደባው ዘግይቶ ከሆነ ግን በግለሰቡ ላይ የሚደርስ ችግር የመ/ቤቱ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

6.5 የመንግሰት ሠራተኛ ያልነበሩትን በሚመለከት ግን ከፐብሊክ ሰርቪስና ከሰው ኃብት ልማት ቢሮ ጋር በመነጋገር የተሟላ ክሊራንስ የያዘ መሆኑ በቢሮው ሲረጋገጥ ወደ ቀድሞ መ/ቤቱ እንዲመለስ ደብዳቤ ሊጽፍለት ይችላል ወይም የስራ ልምዱና የትምህርት ዝግጅቱ በሚፈቅደው የስራ መደብና ደመወዝ ላይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲመደብ ያደርጋል፣

6.6 ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ ተሿሚ የሚመደበው ከሹመት በፊት ይሰራበት በነበረበት አካባቢ ይሆናል፣ ለምሳሌ ክፍለ ከተማ ወዳ ወረዳ ውስጥ ሲሰራ ከነበረ እዚያው ክፍለ ከተማና ወረዳ ይሆናል፣ ማዕከል ይመደባል፡፡

6.7. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 6.4 የተደነገገው ቢኖርም የስራ መደብ በመታጣቱ ምክንያት መመደብ ካልተቻለ ወይም ለስራው አስፈላጊ ነው ተብሎ በበላይ አኳል ከታመነበት እንደየአግባቡ በፐብሊክ ሰርሰቪስና የሰው ኃብልማት ቢሮ ወይም በክፍለ ከተማው ፐብሊክ ሰርቪስ ጽ/ቤት በኩል ቀርቦ በሌሎች በማእከልና በክፍለ ከተማ መ/ቤቶች ውስጥ በሚመጥነው የስራ መደብ ላይ ሊመደብ ይችላል፡፡

6.8. ከላይ በዚህ አንቀጽ ስር የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ከክፍለ ከተማው ስር ካሉት ወረዳዎች ከኃላፊነት ለሚነሱ የመንግስት ተሿሚዎች ምደባው

የሚሰጣቸው በክፍለ ከተማው ፐብሊክ ሰርቪስ ጽ/ቤት ይሆናል፤በማእከል ለሚነሱ ኃላፊዎች ምደባውን የሚሰጠው የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ነው::

6.9.የመንግስት ሠራተኛ የነበረ እና ከሹመት የተነሳ ኃላፊ በዚህ መመሪያ መስረት ሊመደብ ክፍት የስራ መደብ ካልተገኘ ወይም ተመጣጣኝ የስራ መደብ ከጠፋ ዝቅ ባለው የስራ መደብ ላይ ተመድቦ በሚሪት አግባብ ሊደርስበት የሚያሥችለዉን ደመወዙ ይከፈለዋል፡

6.10.ከሹመት ለሚነሱ ምደባ የሚከናወነው በፐብሊክ ሰርቪስ የምልመላና መረጣ መመሪያ ውስጥ በተገለጸው የተፈላጊ ችሎታ መስፈርት መሰረት ብቻ ነው::

6.11.በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ተወስኖ ለክፍለ-ከተማ ወይም ከወረዳ የተነሳ ኃላፊ በማእከል ቢመደብ የስራ መደቡና ደመወዙ በነበረበት ወረዳ ወይም በክፍለ ከተማው ሊመደብበት በሚችለው የስራ ደረጃና ደሞዝ በላይ መሆን የለበትም ወይም ከፍ ባለ የስራ መደብ ላይ መመደብ ክልክል ነው::

## ክፍል ሶስት፤

7. በመንግሥት ፈቀድ የሚማሩ ኃላፊዎች ወደ ት/ቤት ሲገቡና ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ሲመለሱ የሥራ ምደባና የደመወዝ አከፋፈል ሁኔታ፤

7.1 ተሿሚዎች ወደ ትምህርት ሲላኩ የደመወዝ አከፋፈል ሁኔታ፤

7.1.1 የስልጠና/የትምህርት ዕድል ያገኘ ተሿሚ፣ በከተማው ካቢኔ ተወስኖ የሹመት ደመወዝ እያገኘ እንዲማር ካልተፈቀደ በስተቀር ሌላ መደብ የሌለው የደመወዝ ቋት ተከፍቶለት ይማራል፤

ሀ/ ከማዕከል መ/ቤቶች ውስጥ የከተማ ካቢኔ አባል፣ ም/ቢሮ ኃላፊና በዚህ ደረጃ በሹመት ተመድቦ ሲሰራ የነበረ ወይም የክ/ከተማ ሥራ አስፈጻሚና ምክትሉ ወይም በዚህ ደረጃ የተሾሙ ከሆኑ ትምህርታቸውን ጨርሰው እስከሚመለሱ ድረስ ያልተጣራ የወር ደመወዝ ብር 5781 (አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ አንድ ብር) እየተከፈላቸው ይማራሉ፤

ለ/ የክፍለ ከተማ የካቢኔ አባላት ወይም በዚህ ደረጃ የተሾሙ ከሆኑ ያልተጣራ የወር ደመወዝ ብር 4461 (አራት ሺህ አራት መቶስልሳ አንድ ብር) እያገኙ ይማራሉ፤

ሐ/ በወረዳ ደረጃ ዋና ሥራ አስፈጻሚና በዚህ ደረጃ የተሾሙ ከሆነ ያልተጣራ የወር ደመወዝ ብር ቁርጥ ብር 4461 (አራት ሺህ አራት መቶስልሳ አንድ ብር) እያገኙ ይማራሉ:: ሌሎች የወረዳ የካቢኔ አባልና በዚህ ደረጃ የተሾሙና የካቢኔ አባል ያልሆኑ ተሿሚዎች ካሉ ያልተጣራ

የወር ደመወዝ ብር 3908 (ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ብር) እየተከፈላቸው ይማራሉ፡፡

መ/ ሆኖም ግን ከላይ በ7.1 (ሀ-ሐ) የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው የስልጠናውን እድል ያገኘው ተሿሚ ቀደም ሲል ከመሾሙ በፊት በሚሪት ያገኘው የነበረው ደመወዝ ከተጠቀሰው ደመወዝ በላይ ሆኖ ከተገኘ ያንኑ የድሮውን የሚሪቱን ደመወዝ እያገኘ ትምህርቱን ይቀጥላል፡፡ (ለምሣሌ ልዩ የደመወዝ ስኬል ምክንያት በሚሪት የተገኘ ደመወዝ አይቀነስም)

ሠ/ ተሿሚው ከላይ በተገለፀው መሠረት መደብ የሌለው የደመወዙ ቋት ተከፍቶለት ተወስኖለት ወደ ትምህርት ሲገባ ሌሎች እንደ ቤት አበል፣ የሞባይልና የመዘዋወሪያ አበልና የመሳሰሉትን ጥቅማ ጥቅሞችን አያገኝም፣

7.2 ተሿሚዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ የአመዳደባቸው ሁኔታ፤ በየትኛውም ፕሮግራም /በመደበኛ፣ በማታ፣ በክረምትና በርቀት/ ከመጀመሪያ ዲግሪና በላይ ትምህርታቸውን ያሻሻሉት ተሿሚዎች በመንግስት ፈቃድ እንደገና ወደ ሹመት ካልተመለሱ በስተቀር ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ፤ በትምህርት ዝግጅታቸውና በሥራ ልምዳቸው መሰረት በሜሪት የስራ መደብ ላይ ይመደባሉ፡፡

## ክፍል አራት፤

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፤

8. ከመንግሥት መ/ቤት ውጪ ስለሚቀርብ የሥራ ልምድ፤

ከመንግሥት መ/ቤት ውጪ ያገለገሉ ተሿሚዎች በሚሪት የሥራ መደብ ላይ ሲመደቡ የሚያቀርቡት የሥራ ልምድ፤

ሀ/ የሥራ ግብር የተከፈለበት ማረጋገጫ፣

ለ/ የሥራ ጊዜን የሚገልጽ ከ-እስከ፣

ሐ/ የሥራ ኃላፊነት ደረጃን የሚገልጽ እና

መ/ ይከፈል የነበረውን የደመወዝ መጠን የሚገልጽ ሆኖ በሚመለከተው ኃላፊ የተፈረመበትና የተቋሙ ማኅተም ያለበትን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9. ወደ ሌላ ቦታ ስለሚዛወር ወይም ስለሚመደብ ተሿሚ፤

ማንኛውም ከሹመት የተነሳ ተሿሚ ወደ ሌላ መ/ቤት የሥራ ምደባ አግኝቶ ከመሄዱ በፊት ተሿሚ ሆኖ የተረከበውን ማንኛውንም የመንግሥት ሃብትና ንብረት አስረክቦ የተሟላ ክሊራንስ ይዞ መሄድ ይኖርበታል፣ ክሊራንስ ከሌለው ግን ምደባ አያገኝም ለሚደርስበት ጉዳትም ተጠያቂው ራሱ ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት
ልማት ቢሮ

CITY GOVERNMENT OF
ADDIS ABABA PUBLIC AND
HUMAN RESOURCE
DEVELOPMENT BUREAU

ቁጥር 03-ጠ11-40/82/988
Ref. No.

ቀን 22/6/2013
Date

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
- ለአራዳ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት
- ለለሚ ኮራ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በተለያየ ምክንያት ከአመራር የተነሱ ምደባን በተመለከቱ ይሆናል፡

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በሹመት በመንግስት ኃላፊነት ሲሰሩ ቆይተው በተለያየ ምክንያት ከኃላፊነት ሲነሱ በመመሪያው መሰረት ምደባ እንደሚሰጣቸው ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ የክፍለ ከተማው ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት በመመሪያው መሰረት መመደብ ሲገባቸው የተለያየ ምክንያት በመስጠት ቢሮ ምደባ እንዲሰጣቸው የሚላኩ አመራሮች እየተበራከቱ በመምጣቸው ምክንያት ክፍት የስራ መደብ ባለመገኘቱ ያለሥራ ለበርካታ ወራት እየተቀመጡ ይገኛሉ፡፡

ስለዚህ አመራሮች ከሹመት ሲነሱ ምደባ አሰጣጥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት በዚያው በየክፍለ ከተማው ምደባ እንዲሰጣቸው ሆኖ ወደ ቢሮ መላክ የማይቻል መሆኑን እየገለጽን በየክፍለ ከተማው ምደባ ሳይሰጥ ቀርቶ ለአመራሮች መንገላታትና ያለ አግባብ ለሚከፈለው ደመወዝ ኃላፊነቱን የሚወስደው የክፍለ ከተማው ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት መሆኑን ከወዲሁ በጥብቅ እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
- ለቢሮ ኃላፊ
- ለበሰው ሀብት ስራ አመራር ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ
- ለሰዉ ሀብት ስምሪትና መረጃ ዳይሬክቶሬት

አዲስ አበባ፣

☒ 9092
Tel -0118-49-40-91 Fax 57-36-00
www.aacsa.gov.et
አዲስ አበባ
ADDIS ABABA
☎ 55 01 11
E-mail: aacscom@yahoo.com